ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org
ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ
Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band

***የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ***
***ቀን ሚያዚያ 29 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ***

**አላቆም ያለው የኢትዮጵያ ሰቆቃ!**

በዚህ ባሳለፍነው ሣምንት ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ከዳር እስከ ዳር በአንድ ላይ በመውጣት፤ እንደ በግ የታረዱበትን ልጆቹን አሰቃቂ ሞት መሪር ሀዘኑን ተወጥቷል ። በዓለም ዙሪያ የተሰደደው ዜጋ ሁሉ ምሬቱን፤ ሀዘኑን ሲገልጽ ቆይቷል። በበርካታ ኪሎ ግራም የሚመዘን የመታሰቢያ ሻማ በርቷል ። ተቃጥሏል። ለቁጥር የሚታክቱ የተቃውሞ ሰልፎች በዓለም ዙሪያ ባሉ ከተሞች ተካሄደዋል። ሙሾዎች ተደርደረዋል። አንጀት የሚበሉ የሀዘን ግጥሞች ተጽፈዋል ። ኤሎሄ ኤሎሄ ! እየተባሉ ተነብበዋል ። በመላው ዓለም የሚገኙ የሀይማኖት ተቋማት የሀዘን ጸሎት አድርሰዋል ። የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች የውግዘት መግለጫ አትመዋል። ሀገር- ወዳድ ኢትዮጵያውያን ምሁራንም ፤ ቀስቃሽ- አነሳሽ ጽሁፍ ለታረዱት ወገኖቻችን መታሰቢያ አበርክተዋል ።

በሀዘን ልቧ የተሰበረው ፤ አንዲት- እስላም ኢትዮጵያዊት ወጣት ሴት፤ በዕንባ የታጠበውን ፊቷን እያበሰች ፤ ወንጀለኞቹ ን በሚገባቸው ፤ በዐረብኛ ቋንቋ፤ ቅዱስ ቁርዓንን እየጠቀሰች አውግዛቸዋለች ። ስሟ ኢክራም ትባላለች ። የሀገሯ ኢትዮጵያንና የሕዝቧን ፍቅር ለመግለጽ ተንሰቅስቃ አልቅሳለች ። የተመልካቿንም ልብ በልታለች ።

" እናንተ አረማውያን፤ የገደላችኋቸው፤ ሠላሣ ወገኖቻችንን ብቻ አይደለም። መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ጭምር እንጅ " ብላቸዋለች ። እናንት ነጃሳዎች፤ ጀሃነም {ገሃነም} ትገባለችሁ " ብላ ረግማቸዋለች ። ቅዱስ ቁርዓንንና ኤል ሃዲስ መፃሃፍን እየጠቀሰች፤ " ሀበሻን አትንኳት የተዳፈነች እሳት ነችና ታቅጥላችኋለች " ( ከሊሃ ኤል ሀበሽ ወ ህያ ኤል መካን ሚን ወለኣ ) ብላ በድፍረት ተገፍጣቸዋለች። ስሟንም ደፍራ ተነግራ ፤የሚከተልባትን አደጋ ሳትፈራ፤ ቆራጥ ኢትዮጵያዊት መሆኗን አረጋግጣ ነግራቸዋለች ። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም አመስግኗታል ፡፡ ኮርቶባታል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤በተጠቃ ጊዜ፤ በአንድ ላይ ተባብሮ እንደሚነሳም አስመስክራለች። እስላም / ክርስቲያን ሳይል ሁሉም በኢትዮጵያዊነቱ ተባብሮ እንደሚቆም መስክራለች ። ለከሃዲዎቹም ለነ ወያኔዎቹ፤ ዕውነተኛ ኢትዮጵያዊት ማለት ምን እንደሆነች በአደባባይ ነግራቸዋለች ! እስኪበቃቸው !

የሰማዕቱ ክብር አስከሬናቸው፤ ኢትዮጵያዊ ሬሳቸውም እንደ አልባሌ ዕቃ በየበረሃው ወድቆ ቀርቷል ። የት እንደወደቀ፤ ማንም አያውቅም ። የአራዊት መጫወቻ ፤ የአሞራ ሲሳይ ሆኖ ቀርቷል ። ወላጆቻቸውና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን አንጀታቸው አርሮ ቀርቷል ። የሚጽናኑበት ቀን ግን ሩቅ አይሆንም ። ይመጣል ! በያለህበት፤ ተነሳሳ! ተጠራራ፤ እየከተትክ መክት፤ የሀገራችን ሕዝብ ! እየከተቱ መመከት ፤ አኩሪ ታሪክህ ነበር ። ዛሬም ነው ! ወደፊትም ይኖራል !

" በሉ እናንተም ሂዱ፤ እኛም ወደ እናንተ፤ እኛም ወደ ዚያው ነው ፤

ወትሮም መንገደኛ ፤ ጥንትም መራሽ ጀግና ፊትና ኋላ ነው ። "

የኢትዮጵያ ሬሳ ፤ ጥንት በደጓአሌ፤ ወትሮ በኦጋዴን ይቀበር ነበረ

ዛሬ ቀባሪ አጥቶ ሊቢያ በረሃ ፤ የትም ወድቆ ቀረ ።

እንደ ኢትዮጵያ ጀግኖች ፤ እኒያ ሰማዕታት፤

ከጥንት አይደለም ወይ ፤ እንደ ወጡ መቅረት ! "

ጀግንነት የወለል ፤ መሥዋዕት በከንቱ ፤ ዜግነት የበለል ፤

ትውልድ መች ይተኛል ፤ ትጥቅስ መቼ ይፈታል ፤

ጥላት አንተርሶ ፤ ብድሩን ሳይመልስ ፤ እዳውንም ሳይከፍል ፤

አንገቱን አቅንቶ ፤ ቁጭቱን ተውጥቶ ፤ ጥቃቱን ሳይመልስ "

እያለ ተቅምጧል፤ በየቤቱ ! መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ለጊዜው የሚይዘው፤ የሚጨብጠው ፤ አጥቶ ቀርቷል !

በጣም የሚገርመውና የሚያሳዝነው ግን መላው ዓለም ፤ በሊቢያ በረሃ፤ በወገኖቻችን ላይ የተፈፀመውን ግድያ እያወገዘ፤ ሀዘኑን በሚገልጽበት ጊዜ፤ የወያኔ ጉደኞች፤ "ኢትዮጵያውያን መሆን

አለመሆናቸውን ገና በማጣራት ላይ ነን " ማለታቸው ነበር ። ወትሮውኑም ቢሆን፤ በሞተ- ከዳ ተመልምሎ ፤ በአጣ - ቆዩኝ ደረጃ ከተቀመጠው የወያኔ ፍራሽ አሳዳሽ ምንደኛ ግልስብ፤ ከዚህ የተለየ ነገር እንደማይጠበቅ ግልፅ ነበር ። መቸውንም ቢሆን፤ የራሱን ሰብ ዕና የማይጠብቅ ሰው ፤ ስለ ሀገር ያስባል ተብሎም የሚጠበቅ እንዳልሆነ የታወቀ ነው ። በዛሬው ጊዜ፤ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር፤ መሪ አልባ መሆኗ ብቻ ሳትሆን ፤ የራሷም ኅልውናም ቢሆን፤ በውጭ -ነፍስ - ግቢ ነፍስ መካከል ሆና የምትጠራሞት ምድር እንደሆነች ያመለክታል።

"በሬ ካራጁ ጋር ይውላል " ሲባል የነበረው ብሂል ቀርቶ፤ ዛሬ፤ ከምትታረድብት ቦታ ለመድረስ፤ ገንዘብ እየከፈልክ ተሰደድ ! ተብሎ ታውጇል ። ማነኛውም ጤናማ ኢትዮጵያዊ ወጣት ፤ ከሁሉም በላይ የሚወስደው የመጀመሪያው ምርጫ ፤ ነፍሱን ሸጦም ቢሆን ፤ ከሀገሩ ወጥቶ መሰደዱን ሆኖ ቀርቷል ። ተምሮ ፤ ሥራ ይዞ፤ ራሱንና ቤተስቡን ለመርዳት የነበረው ጉጉትና ብሩኅ ተስፋ የበረሃ እንብልብሊት ( ሚራዥ) ሆኖ ቀርቶበታል ። የኢትዮጵያ ሰማይ- ምድር ጨለምተኝነት የሰፈነበት እንጅ፤ ብሩኅ ተስፋ የሚታይበት አልሆነለትም።

የራሱን፤ የቤተስቡን፤ የኅበረሰቡንና የሀገሩን ተስፋ፤ ድጋፍና ትብብር አግኝቶ፤ በራሱ ምኞት፤ ችሎታና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ውጤት ለያስመዘግብ አልቻለም ። በመሆኑም፤ በመንገድ ላይ የሚያጋጥመውን ስቃይና መከራ መቀበልን፣ በባዕዳንም እጅ ቢሆን፤ እየሄዱ መታረድን መርጦ ቆርጦ ይሰደዳል ። በጣም አስደንጋጭና አስፈሪ የሆነው ደግሞ፤ አሁንም፤ የሊቢያው ግድያ ከተፈፀመም በኋላ እንኳን ፤ ከሀገር መሰደዱን እንዳማያቋርጥ ወስኗል ። ለዚህ ምርጫ ደግሞ ወያኔ፤ ምክንያትና ግንባር -ቀደም ተባባሪ ሆኖለታል ።

ዛሬ፤ ከሀገር የሚሰደዱትን ወጣቶች የሚገፋፋና የሚያበረታታ፤ የወንበዴዎች ድርጅት ተቋቁሞ የሰውን ልጅ እንደ ኮንትሮባንድ ዕቃ በድብቅ የሚያጓጉዝ አስተላላፊ( ስማግለር) መስመር ተዘርግቷል ። ይህ መስመር የተዘረጋው ከአዲስ አበባ ተንስቶ በመተማ አድርጎ ፤ የኢትዮጵያን ድምበር ተሻግሮ በመሄድ፤ የሱዳን አዋሳኝ የሆነውን የገላባትን ከተማ አልፎ ካርቱም ይደርሳል። ከዚያ በኋላ፤ የሱዳንንና የሊቢያን በረሃዎች አቋርጦ፤ በሜዲቴራንያን ባኅር ጠረፍ አድርጎ፤ ወደ ተለያዩ የአውሮፓ ሀገሮች የሚያስተላልፍ ትልቅ የወንጀሎኞች ማፍያ ድርጅት ነው ። በዚህ ሂደት፤ ወያኔ የለበትምና አያውቀውም ማለት አይቻልም ። የወያኔ መረጃ ትብበርና ቅንብር ከሌለበት ማነኛውም ወንጀል እንደማይፈፀመ የታወቀ ነው። የገንዘብ ክፍያው ደላላዎችም ወያኔዎቹ እንድሆነ ሁሉም የሚያውቀው ሆኗል።

ክፍያውም እንደሚከተለው ነው ፡፡

1ኛ. ከአዲስ አበባ እስከ መተማ ደረስ ላለው ጉዞ 500 የኢትዮጵያ ብር ያስከፍላሉ ፡፡

2ኛ. አዲስ አበባ ለአለው የሱዳን ኤምባሲ 10 000 ( አስር ሽህ የኢትዮጵያ ብር) ወይም 500 ዶላር ይከፈላል ፡፡

3ኛ. ከሱዳን ተነስቶ ሊቢያ ለመድረስ፤ ከ 45 ሽህ እስከ 50 ሽህ የኢትዮጵያ ብር ወይም ከ 2175 እስከ 2400 የአሜሪካ ዶላር ያስከፍላሉ ፡፡

4ኛ. ከሊቢያ የባህር ጠረፍ ( ሜዲቴራንያን ባህር ) ተነስቶ ወደ አውሮፓ ሀገሮች ጣሊያን ፤ ፈረንሳይና ጀርመን ለመላክ 80 ሽህ የኢትዮጵያ ብር ወይም 3850 የአሜሪካ ዶላር ያስከፍላሉ ፡፡

5ኛ. በአብዛኛው ፤ የክፍያው መንገድ የሚፈፀምው ፤በስልክ እንደሆነ ይታወቃል። ይኸም ዘዴ የተመረጠው፤ ያድራጊዎቹን ማንነት ላለማጋለጥ የሚደረግ ጥንቃቄ እንድሆነ ይገመታል ፡፡

በዚህ ዓይነት ህገ - ወጥ በሆነ መንገድ የሚደረገው የወንጀል አፈጻጸም ፤ ምናልባትትም ከ 150 ሚሊዮን ዶላር በመት የሚያስገባ ንግድ ነው፡፡ የሰውን ልጅ፤ ለዕርድ፤ የሚያቀርብ ፤ ለጭዳ የሚልክ የነፍስ-ገዳዮች አባሪ-ተባባሪ ወንጀለኛ ደርጅት ነው። የኢትዮጵያን ወጣቶች ከሀገራቸው እያስወጣ ፤ እንደ ፍሪዳ ከብት ለዕርድ ያቀርባቸዋል ፡፡ መንግሥት የሌላት ሀገራችንም፤አዳጊ ወጣቶቿን፤ ከአሰቃቂ ዕልቂትና ግድያ ሊታደጋቸው የሚችልላት ተቋምም ሆነ ድርጅት አጥታለች።

ጥቃቱ ሲደርስና ጥፋቱ ሁሉ በሀገርና በሕዝብ ላይ ሲደርስ ግን በግብታዊነት ሁሉም እየደነገጠ ሀዘኑንና ለቅሶውን ይገልጻል ፡፡ ከዚያ ያለፈ ቁም ነገር መስራት እስካሁን አልተቻለም ፡፡

ሰላማዊ ሠልፍ ከመውጣት፤ የሀዘን መታሰቢያ ሻማ ከማብራት፤ ፀሎተ- ፍትሃት ከማድረስ፤ ሙሾ ከመደርደርና ደረትን ከመደለቅ ያለፈ ቁም ነገር መስራት አልተቻለም ፡፡ ! ተባብረንና ተስማምተን ፤ ተደማምጠንና ተማምነን በጋራ ለመወያየት የሚያስችለንን ሁኔታ እንኳን ማምጣት አልተሳካልንም። የባቢሎን ግንብ ሰሪዎች ሆነን ቀርተናል ፡፡ እንደ ሎጥ ሚስት የጨው ሃውልት ሆኖ፤ ደርቆ ለመቅረት እንሮጣለን ፡፡ ሁሉም ፤ እያንዳንዱም፤ የየራሱን የየግል ዓርማውን በግለሰብ ደረጃ እያውለበለበ፤ እርካታን ወዶ ተቅምጧል ፡፡

ሁሉም በየቤቱ ፤" **ከእኔ ወዲያ ጎራሽ ፤ እህል አያበላሽ !** " ከእኔስ የበለጠ ማን ነው ለኢትዮጵያ ችግር መፍትሄ ፈላጊ ? ብሎ ሁሉ በሩን ዘግቶ ተቀምጧል ። በራፉን አንኳኩቶ ገብቶ የሚያስረዳው ዘመድ - ወዳጅ እንኳ አልተገኘም። ተናጋሪና አድማጭ፤ መካሪና ተባባሪ ባለመገጣጠማቸው፤

**" እየነገርናቸው እያረጉት ዋዛ ፤**

**ከተለበለበው የተላጠው በዛ** ! " የሚል እንጉርጉሮ በዝቷል ።

የሀገራችን ጥፋትና የሕዝባችን መከራ፤ ጥልቀቱ ፤ ክብደቱና ስፋቱ የቱን ያኀል እንደሆነ እንኳን መገንዘብ ተስኖናል ። ያ ባይሆንማ ኖሮ፤ ወደ መፍትሄው ፍለጋ ፤ በጋራ እንተባበርን ነበር ። አንድ መሠረታዊ ጉዳይ አፅንኦት ተሰጥቶበት ሁሉም ካላሰበበትና መቀራረብ እስካልተቻለ ድረስ፤ የሀገራችን ጉዳይ ዘላቂ መፍትሄ ያገኛል ተብሎ አይታሰብም ። በዚህም ተባለ በዚያ፤ የሚከተሉትን ዕውነታዎች አብክሮ ማሰተዋል ለሀገራችን ችግሮች አፈታት የማዕዘን ድንጊያውች ሆነው ሊቆጠሩ ይገባል ።

1ኛ፣ ኢትዮጵያ የብዙሃን ብሄሮች መኖሪያ ሀገር እንደ መሆኗ፤ ለችግሮቿ መፍትሄ ፍለጋም፤ የሁሉንም ተሳትፎ ትፈልጋለች።

2ኛ .የዜጎቿ ጉራማይሌነት፤ የጥንካሬዋና ሀብቷ ምንጮች እንጅ፤ የድክመቷ፤ የድህነቷና የችግሮቿ ምክንያቶች አይደሉም።

3ኛ. የሁሉንም ተሳትፎ ያካተተ መፍትሄ አፈላለግ ዘዴ፤ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት ሊጥል ይችላል ። አግላይ የሆነ የመፍትሄ ፍለጋ፤ የትም እንዳላደረሰ የአስካሁኑ ተመክሮ ማስረጃ ይጠቀሳል ። በብዙሃኑ እምነት፤ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኗል ለማለት የሚያስችለው፤ አሳታፊና ( Participatory Democracy ) የሚሰራ( Functional Democracy) እውን ሲሆን ብቻ ነው።

4ኛ. ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ፤ በግድ ልዩ ልዩ ተቋማት መመስረትና እነርሱንም ፤ አክብሮ መጠበቅ አስፈላጊ ነው። በተለይ ደግሞ፤ የአራት ተቋማት መኖር አጠያያቂ አይሆንም ። እርሱም---

ሀ). የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤

ለ). ነፃና ገለልተኛ ፍርድ ቤት፤ የፍትህ ሥርዓት

ሐ) ሥልጣኑ በህግ የተገደበና፤ ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ ለሀገሪቱ ምክር ቤት የሆነ አስፈፃሚ ክፍልና

መ). ነፃ ፕሬስ ናቸው ።

የእነኝህ ነፃ ተቋማት መኖር ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ። የእነኝህ ነፃ ተቋማት አለመኖር፤ እስካሁን ድረስ፤ ሀገራችን የአምባገነን ሥርዓት ሰለባ ሆና ቆይታለች። ኢዴሞክራሲ አገዛዝን አስወግዶ፤ ፤ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካትና ነፃና ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን መመስረት አማራጭ አይኖረውም ።

5ኛ. አንድነቷ ተጠብቆ ነጻነቷንና እድገቷን ዋስትና ለማረጋገጥ ካስፈለግ፤ በእነኝህ መሠረታዊ ራዕዮች ዙሪያ ተሰባስቦ በኅብረት ከመታገል የተሻለ/ የተለየ ብልሃትና አማራጭ ለጊዜው ሌላ ዘዴ አልተከሰተም ።

ይህንን የቤት ሥራ ሰርቶ፤ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ካልተጀመረ፤ የሀገራችን መከራና ስቃይ ሊያባራ አይችልም። የህዝቡም ስደት ይቀጥላል። ግድያውም በሀገር ቤት ብቻ ሳይሆን፤ በዓለም ዙሪያ ከአሁኑ በበለጠ አሰቃቂ መልክ ይካሄድብናል ። " **ሞኝን እናቱም ብትሆን አትወደውም** " እንዲሉ፤ እኛ ብልሆች ሆነን ከልተባበርንና የራሳችንን ችግር፤ ራሳችን መፍታት ካልቻልን፤ በሌሎች ርዳታ፤ ሀዘኔታና ርኅራኄ ልንተማመን በጭራሽ አይገባንም። የፖለቲካ ትግል፤ በወሳኝነት ሊጠናቀቅ የሚችለው፤ የኃይል ሚዛኑን፤ ባስተማማኝ ደረጃ ከወያኔ እጅ ነጥቆ፤ በሕዝብ እጅ ሲገባ ብቻ ነው። የፖለቲካ ትግል፤ አልፋና ዖሜጋው፤ የኃይል ሚዛን ጉዳይ ነው። ለጊዜው የአምባገነኑ አገዛዝ በሥልጣኑ ውር-ውር እያለ ፈርጠም ብሎ የሚፈራገጥ ቢመስልም ፤ እንደ ሀረግ ሬሳ ተከል፤ በምዕራባውያን ታዛ ተንጠልጥሎ የሚልፈሰፈስ የጠወለገ ቅጠል ማለት ነው ። ወያኔ፤ ዱሮም ያልነበረው ሕዝባዊ መሠረት አሁን በህይወት በፍፃሜው ወቅት ሊያገኝ አይችልም ። ተባብሮ ተስማምቶና ተማምኖ ይህንን ከይሲ ዘረኛ አጋዛዝ፤ አሁኑ ማስወገድ ካልተቻለ ፤ የማይችልበት ምክንያት ደግሞ ሊኖር አይችልም፤ የደም ዕምባ የምታለቅሰው ሀገራችን ፤ ዕምባዋ እየነጠፈ፤ ደሟ እየተንጠፈጠፈ ይቀጥላል ።

ይህንን ሀገራዊ አበሳ ለማስቆም፤ ዘረኛው የወያኔዎች አገዛዘ መወገድ አለበት።

" **አገሩን በሚገባ ያገለገለ፤ / የሚያገለግል፤ ትውልዱን መቁጠር አያስፈልገውም ።** "

**ብሏል ፈረንሳዩ ቮልቴር**

የዛሪይቱ ኢትዮጵያ፤ በዘር፤ በትውልድና በቋንቋ ላይ በተመሰረተ አገዛዝ ስር ወድቃለች ።ይህ ከይሲና ኋላ ቀር የሆነ ሥርዓት ነው ። የነገዋ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ችሎታን መሠረት ያደርገ አስተዳደራዊ ሥርዓት ( Meritocracy ) እንጅ፤ በዘር ላይ የተመሰረ( Ttribalism/ Racism) አገዛዝ አይደለም ።

ይህንን ለማምጣት የሚፈልግ ሁሉ ተባብሮና ተስማምቶ ከመታገል የተለየ አማራጭ አይኖረውም ። የሀገራችን ኅልውና፤ ነፃነትና ብልፅግና ሊረጋገጥ የሚችለውም በዚህ መንገድ ነው ። ዘለዓለም በዘረኞች አገዛዝ እየተዋረዱ የደም ዕምባ ከማልቀስ; ባለፈው ሳምንት፤ በሊቢያ በረሃዎች ፤ ለዕምነታቸውና ለኢትዮጵያዊነታቸው የደም መሥዋ ዕት እንደከፈሉት ወገኖቻችን፤ እኛም የሚጠበቅብንን የህይወት ዋጋ በመክፈል፤ ሀገራችንን አናድነን፤ ነፃነታችንን ማስከበር ይጠበቅብናል ። ያን ጊዜ ነው፤ የኢትዮጵያ ደም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚቆመው ።

ወያኔን በሁሉ መንገድ ታግለን እናስወግደው!!

ጸረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም !

በትግላችንና ድላችን ተከብራ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !!